# ለሰማዕታት ታሪክ ዘብ እንቁም!

የአሲምባ የፓልቶክ ክፍል የተቋቋመበት አንዱ ዓላማ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና ዴሞክራሲያዊ መብት ሲታገሉ የወደቁ ሰማዕታት ታሪካቸው እንዳይበረዝና ለሃገራቸው ያደረጉትን ተጋድሎ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ ነው ። በዚህም ምክንያት በተለያየ ጊዜ የደርግ ኢሠፓ ወንጀሎኞች የንፁህንን ደም ማፍሰሳቸው ትክክል መሆኑን በማመን ፋሺሽታዊ ተግባራቸውን በሕብረተሰቡ ውስጥ በተሳሳተ መንገድ እውነታውን አጣመው ማስተላለፍ መሞከራቸው የሚታወስ ነው ።

በአሁኑ ወቅት በተለይ እጃቸው ላይ የንፁህን ደም ያለባቸው ነፍሰ ገዳዮች በፓልቶክ ማን ያውቀናል በማለት ሲፎክሩ ይደመጣሉ ። የወያኔ ዘረኛ መንግስት በፈጠረላቸው የዘር ድርጅቶች በመሰግሰግ ኢሕአፓን ለማጥፋት ከማንኛውም በላይ ጥረት እያደረጉም እንደሆነ እየታዘብን ነው። በተለይ በወያኔና በመንግስቱ ደጋፊዎች የተጠናከረው የሲውዘርላድ የቅንጅት የፓልቶክ ክፍል መሪዎች በኢሠፓ ከፍተኛ አባልነታቸው የሚታወቁ፣ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ከወያኔ ካድሬዎች ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚገኙ መሆናቸው ለብዙዎቻችን ግልፅ ነው ።

በተለይ ባለፈው ሰኞ ወይዘሮ ገነት አየለ ከሚባሉት የፋሽሽቱን የመንግሥቱን ታሪክ ከጻፉ ጋዜጠኛ ጋር ቃለ መጠይቅ ከአደረጉ በኋላ በተደረገው ውይይት ቀይ ሽብር ትክክለኛ መሆኑንና መንግሥቱ ደግሞ ጀግና እንደሆነ ከቤቱ መሪዎች ሳይቀር ይነገር እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን ፣ መንግሥቱን እንደገና ወደ ሥልጣን ለማምጣት ጥረት እንደሚያደርጉ በአደባባይ ሲገልጡ እንደነበር የሚታወስ ነው ።

አሲምባ የፓልቶክ ክፍል የፋሺሽቱን የኢሠፓ መንግሥት ወደ ሥልጣን ለማምጣት የሚደረግ ትግልን የሚዋጋ መሆኑን በተደጋጋሚ ግልጽ ስናደርግ ቆይተናል ። የወያኔን መንግሥት የምንቃወመው ፋሽሽቱን መንግሥቱን ለምን ከሥልጣን አስወገዱት በሚል ሳይሆን የሀገራችንን ልዕልና የሚፃረር ዘረኛ የሆነ ፀረ ዴሞክራሲ መንግሥት በመሆኑ ነው ።

የአሲምባ የፓልቶክ ክፍል አሁን በድጋሚ ደርግ ኢሠፓን በመደገፍ በተዘዋዋሪ ወያኔን ሥልጣን ላይ ለማከረም የሚደረገውን ጥረት ሙሉ በሙሉ ይዋጋዋል ። እነዚህ የቀይ ሽብር ኮኮቦች እንደ ቀልቤሳ ወደ ፍርድ የሚቀርቡበትን መንገድ ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል ።

አሲምባ የፓልቶክ ክፍል በመንግሥቱና በወያኔ ደጋፊዎች የታጀለውን የሲውዘርላንድ የፓልቶክ ክፍል በእንግድነት እየተገኙ ይህንን ፀረ ሕዝብ ፣

ፀረ ዴሞክራሲ የሆነውን እንቅስቃሴ መደገፍ ሃገራችንን ለበለጠ መከፋፈል መገፋፋት መሆኑን እያሳሰብን እያንዳንዱ ግለሰብ እዛ ከፍል ከመቅረቡ በፊት ይህን ጉዳይ ሊመዝነው እንደሚገባ ልናሳስብ እንወዳለን ።ይህንን ተግባር የሚጠነስሱት በሲውዘር ላንድና በእንግሊዝ የሚገኙተን ፋሽስቶች ለማጋለጥ ወደ ኋላ እንደማንልም ልናሳስብ እንወዳለን ።

በተለይ የአሁንም ይሁን የቀድሞ የኢሕአፓ አባለት ፣ የምትወዷቸው አባሎቻችሁ በቀይ ሽብር የተሰውባችሁ ግለሰቦች ፣ ፋሽስቶች በድጋሚ ወደ ስልጣን እንዳይመጡ የምታስቡ ግለሰቦች ይህን አሰከፊ ተግባር ለመታገል ከጎናችን እንድትቆሙ በአክብሮት እንጠይቃለን ።

በፋሽስቶች ከርሰ መቃብር ላይ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ትመሰረታለች።

ኢትዮጵያዊነት በትግላችን ያለጥርጥር ያቸንፋል!
ነፍሰ ገዳይ ፋሺሽቶች ይጋለጣሉ!

የአሲምባ ውይይት መድረክ